# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 1 ቁጥር 09 ነሐሴ 30 ቀን 2011 ዓ.ም
በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## ፍትህ እና ማኅበራዊ ፍትህ



# የኢዜማ ሕዝባዊ ስብሰባዎች ዓላማ

ድርጅት ሰዎች በየግላቸው ጥረት ቢያደርጉ ሊያሳኳቸው የማይችሉ ትላልቅ ግቦችን ለማሳካት ተግባሮቻቸውን የሚያስተባብሩበት መሣሪያ ነው።

ማንኛውም ዘመናዊ ድርጅት ቢያንስ የሚከተሉት አምስት ነገሮች ሊኖሩት ይገባል:

(1) የጋራ ዓላማ ያስተሳሰራቸው ሰዎች (አባላት ወይም ሠራተኞች)፣
(2) የተለያዩ ንዑስ ዓላማዎች ያስተሳሰራቸው መደበኛና ኢመደበኛ ቡድኖች
(3) ዕውቀትና ቴክኖሎጂ፣ (
(4) ሥርዓቶች - ድርጅታዊ መዋቅር፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎችና ልማዶች እና
(5) ንብረቶች።

ጠንካራ ድርጅት እንዲኖር ከላይ የተዘረዘሩት አምስቱም ከፍተኛ ሚና አላቸው። የድርጅት ጥንካሬ በአባላቱ ጥራትና ቁርጠኝነት፤ በውስጡ በሚፈጠሩ ቡድኖች መካከል ያለው መናበብና መግባባት፣ ድርጅቱ ባካበተው እውቀት መጠን፤ በገነባው ድርጅታዊ መዋቅር፣ በሚከተለው ሥርዓት እና በሚያስተዳድረው ድርጅታዊ ንብረት መጠን ይወሰናል።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ ፓርቲ (ኢዜማ) እጅግ ግዙፍ የሆነ ራዕይ ነድፎ የተነሳ ድርጅት ነው።

ኢዜማ የኢትዮጵያ ሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነት እንዲረጋገጥ፤ ለሀገራችን ተስማሚ የሆነ ፌደራላዊ ሥርዓት እንዲኖር፤ እድሜው ለምርጫ የደረሰ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በተሳተፈበት ምርጫ በሚመረጥ ፕሬዚዳንት የፌደራል መንግሥት የሚዋቀርበት የፓለቲካ ሥርዓት እንዲኖር፤ በማኅበራዊ ፍትህ እሳቤ የተቃኙ የፓለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ፖሊሲዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ፤ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ በማድረግ ዜጎች ያለተፅእኖ ተሳትፎ ያደረጉበት፣ የመንግሥትን ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ የፓለቲካ ሥርዓት እንዲገነባ፤ ፓርቲና መንግሥትን ማደባለቅ እንዲቀር፤ ፍትህ፣ ነፃነት፣ የሀገር አንድነትና ዴሞክራሲ እንዲሰፍኑ፤ ሀገራችን እንድትበለጽግ፤ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በዜግነቱ የሚኮራባት ሀገር እንድትሆን የሚታገል ፓርቲ መሆኑ በፕሮግራሙ ላይ ተዘርዝሯል። ይህ ግዙፍ ዓላማ ነው።

ይህንን አባላቱ፣ ደጋፊዎቹ እና አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጓጓለትን ግዙፍ ዓላማ የማሳካት ብቃት ያለው ድርጅት መገንባት ራሱን የቻለ ትልቅ ግብ ነው።

በዚህም ምክንያት ኢዜማ ችግሮችን በልጦ መገኘት የሚችል፤ በየጊዜው ራሱን የሚያሳድግ፣ አባላቱ ለድርጅቱ ግቦች መሳካት የሚያስፈልጋቸውን እውቀትም ሆነ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ ሁኔታዎች የተመቻቹበት ተቋም ማድረግ ይኖርብናል።

ከዚህ ዓላማ በመነሳት ነው የኢዜማ አመራሮች አቅም በፈቀደ መጠን ሕዝባዊ ውይይቶችን፣ ስልጠናዎችና ሴሚናሮችን እያደረጉ ያሉት። ሰሞኑን በአዲስ አበባ እና በደሴ የተደረጉ ስብሰባዎች ዓላማዎችም ይኸው ነው። ወደፊትም ተመሳሳይ ውይይቶችና የእርስ በርስ መማማሪያ መድረኮች በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች ይደረጋሉ። በሁሉም የምርጫ ወረዳዎች የተቋቋሙና ወደፊትም የሚቋቋሙ ጽ/ቤቶቻችን ሥራዎች ከላይ የተጠቀሰውን ዓይነት ዘመናዊ ድርጅት ለመገንባት ተግተው ይሠራሉ። ኢዜማ የሚያዳምጥ፣ የሚያስብ፣ የሚያቅድ፣ የሚተገብር እና ውጤት የሚያመጣ ድርጅት ለማድረግ ተግተን እንሠራለን።

የኢዜማ አባል መሆን ማለት ሕይወት ያለው፣ የሚማር፣ የሚያድግ፣ ሠርቶ የሚያሠራ ድርጅት አባል መሆን ማለት ነው። የኢዜማ አባል መሆን ማለት ለዕውቀት መቅረብ ማለት ነው። የኢዜማ አባል መሆን ማለት ኢትዮጵያን የማዘመን ትልቅ ፕሮጀክት አካል መሆን ማለት ነው። የኢዜማ አባል መሆን ማለት ለገዛ ራስ፣ ለቤተሰብ፣ ለጎረቤት፣ ለማኅበረሰብ፣ ለሀገር ዘላቂ ዕድገት አስተዋጽዖ ማድረግ ማለት ነው።

እራሳችንን እና ሀገራችንን ለማበልፀግ ጠንካራ ድርጅት ያስፈልገናል፤ ለጠንካራ ድርጅት መኖር ደግሞ የብቁ አባላትና ደጋፊዎች መኖር ወሳኝ ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያዊያን በያላችሁበት ኢዜማን እንድትቀላቀሉ፤ በስብሰባዎቻችን እንድትገኙ፤ ምክር እንድትሰጡን፣ እና ስንሳሳት እንድትወቅሱን አበክረን እንጠይቃለን። ተደጋግፈን ሀገራችንና ሕዝቧን ወደ ዓለምነው ብሩህ ግብ እናደርሳለን።

# “የሚያጠናክሩን የተቃውሞ ድምፆች ናቸው!”

የኢዜማ ምክትል መሪ አንዱዓለም አራጌ
ነሐሴ 30 ቀን 2011 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በደሴ ከተማ የኢዜማ ምክትል መሪ አንዱዓለም አራጌና የሕዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ናትናኤል ፈለቀ በተገኙበት ሕዝባዊ ስብሰባ አደረገ፡፡

የኢዜማ አባላት እና ደጋፊዎች እንዲሁም ኢዜማን የማይደግፉ የከተማዋ ነዋሪዎችም ጭምር በስብሰባው ተገኝተው ጥያቄ እና አስተያየቶቻቸውን ያለገደብ ማቅረባቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በስብሰባው ላይ የተወሰኑ ወጣቶች ተገቢ ያልሆነ ሥነ - ምግባር ቢያሳዩም ከአዳራሹ ሳይወጡ ሃሳባቸውን በነጻነት ያለገደብ በሁለት ዙር እንዲያቀርቡ እንደተፈቀደላቸው የፓርቲው ምክትል መሪ አቶ አንዱዓለም አራጌ የገለጹ ሲሆን በስብሰባው ላይ አብዛኛውን ጥያቄ እንዲጠይቁ እድል የተሰጠው ኢዜማን ሊቃወሙ ለመጡት መሆኑንም አሳውቀዋል፡ ፡ “ለምን መጣችሁ? እስካሁን ባለው ሀገራዊ ሁኔታ ለምን ዝምታን መረጣችሁ?” የሚሉ ዓይነት ይዘት ያላቸው ጥያቄዎች መሰንዘራቸውን በመጥቀስ ከመድረኩም ኢዜማ ከተመሠረተ የ3 ወራት ጊዜ ብቻ እንዳስቆጠረ፣ ኢዜማ ከተመሠረተ ጀምሮ 16 የፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ጥናቶችን ማስደረጉን እዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ 547 የምርጫ ወረዳዎች መካከል 400 በሚጠጉት ላይ የምርጫ ወረዳ መዋቅሮችን ሲያደረጅ መቆየቱን እ የፓርቲውን የገንዘብና የሰው አቅም እያጠናከረ እንደነበር አሁን ግን ከኅብረተሰቡ ጋር በቅርበት የመገናኘት ሥራ መሥራት እንደተጀመረ በመጥቀስ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

‹‹በዕለቱ ስብሰባውን ለመረበሽ የተንቀሳቀሱ ልጆች እንደነበሩ ወደ አዳራሹ እንዲገቡ አድርገን የፈለጉትን እንዲጠይቁ አድርገናል፡፡ ከመካከላቸውም በሳል የሆነ ጥያቄ ያነሱ ወጣቶች ነበሩ፤ በዚህም ሊመሰገኑም ይገባል፡፡ የሚደግፉትን ብቻ ሳይሆን የሚቃወሙንም እንፈልጋለን፡፡ የሚያጠናክሩን የተቃውሞ ድምፆች ናቸው!›› ብለዋል ስብሰባውን የመሩት የኢዜማ ምክትል መሪ አንዱዓለም አራጌ፡፡ በደሴው ውይይት ላይ በብሔር ፖለቲካ የተሰበሩ ወጣቶችን በማስተዋላችን አዝነናል ያሉት ምክትል መሪው፣ የተሰበሩትን ልጆች ልንረዳቸውና ልናግዛቸው ይገባልም ብለዋል፡፡

በክልሉ ላይ ኢዜማ በደንብ ከሠራ በምርጫ እንደሚያሸንፍ አንዱዓለም አስረግጠው “ኢዜማ ዝም አለ! ሕዝብን አያነጋግረንም!” የሚሉ ወገኖች ከፓርቲው ብዙ ስለሚጠብቁ እንደሆነ እደሚረዱ፣ የሕዝቡን ጥያቄ አንድ በአንድ ለመመለስ እንደሚጥሩ እና የሚታረም ነገር ካለም ፓርቲው እራሱን እያረመ እንደሚሄድ አስረድተዋል፡፡ ከመጠቋቆም ይልቅ መደጋገፍ ይሻላል ያሉት ምክትል መሪው ኢዜማ አሁን እየሄደበት ያለው መንገድ ከግብታዊነት በፀዳ በማድረግ ለውይይት እድል የሚሰጥ እና ኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ የማድረግ ዓላማ ላይ የማይደራደር ፓርቲ እንደሆነ አፅንዖት ሰጥተው አስረድተዋል፡፡


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ነሐሴ 30 ቀን 2011 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ፍትህ እና ማኅበራዊ ፍትህ

## 1. መንደርደሪያ

ፍትህ ሰዎች ተዛዝነው፣ ተሳስበው እና ተረዳድተው እንዲኖሩ የሚያደርግ የበጎ ሥነምግባር መርሆች ስብስብ ነው። የሰዎች ማኅበር ማለትም "ማኅበረሰብ" ከእንስሳት ማኅበር የሚለየው "በጎ" እና "በጎ ያልሆኑ"፤ "ተቀባይነት ያላቸው"፤ "ተቀባይነት የሌላቸው" እና "ሚዛናዊ የሆኑ" እና "ሚዛናዊነት የጎደላቸው" አሠራሮች የሚለዩበት ድንበር መኖሩ ነው። ይህ ድንበር ስላለ እንደማኅበረሰቡ ወግና ባህል ፍትህዊ የሆኑ ነገሮችን ፍትህዊ ካልሆኑ ነገሮች መለየት ይቻላል።

ማኅበራዊ ኑሯቸውን በሚያስደንቅ ሥርዓት አደራጅተው የሚኖሩ እንስሳት ያሉ ቢሆንም በእውቅ (consciously) ሊለወጥ የሚችል ሥርዓት ያለው ፍጡር ሰው ብቻ ነው። ለምሳሌ፣ የጉንዳን ሠራዊት ሰልፍ አሳምሮ ይጓዛል፤ ተጋግዞ ጠንካራ መኖሪያ ይገነባል፤ ስንቅ ያከማቻል፤ ያከፋፍላል፤ የሠራዊቱ አባል የሆነ እያንዳንዱ ጉንዳን የሚያበረክተው አስተዋጽዖ አለው። ይሁን እንጂ ይህ የሚሆነው ግን በእውቅ በተገነባ ሥርዓት ሳይሆን ተፈጥሮ በቋሚነት በሰጠቻቸው የሥራ ድልድል መሠረት ነው። ማን "አዛዥ" ማን ደግሞ "ታዛዥ"፤ ማን አጥቂ ማን ተከላካይ እንደሚሆን በተፈጥሮዓቸው የተወሰነና የማይለወጥ ነው። የንብ መንጋም እንደዚሁ ነው፤ አንዷ ለንግሥትነትና እናትነት፤ ከፊሎች ለአውራነት፤ ከፊሉ ለጥበቃ፤ በርከት ያሉት ለአገልጋይነት ተፈጥረዋል፤ ይህንን ተፈጥሮ ሊቀይሩት ቀርቶ ሊያሻሽሉት እንኳን አይችሉም። ተፈጥሮዓቸው በመሆኑ ይህ ዓይነቱ የኃላፊነት ድልድል ፍትህዊም፣ ኢፍትህዊ ተብሎ ሊመደብ አይችልም።

ሰው በማኅበር ሲኖር ግን ራሱን ያደራጀው ከተፈጥሮ አውድ ወጥቶ ነው። ሰው ሲፈጠር ጥቂቶች ለመሪነት፣ ብዙዎች ለተመሪነት ተብለው አልተፈጠሩም። ተፈጥሮ ከፊሉን ጭሰኛ፤ ከፊሉን ግንበኛ፣ ከፊሉን አናጢ፣ ከፊሉ ነጋዴ አድርጋ አልፈጠረችውም። ተፈጥሮ የተወሰኑ የሰው ዓይነቶችን ለሀብታምነት፣ የተቀሩትን ደግሞ ለድህነት አልፈጠረችም። ይህ ሁሉ የሆነው ሰው በፈጠረው ማኅበራዊ መስተጋብር ነው። መስተጋብሩ በአብዛኛው ሰው ተቀባይነት ካለው እና ሚዛናዊ ከሆነ "ፍትህዊ" ነው ብለን አዎንታዊ እውቀና እንሰጠዋለን በዚሁ እንዲቀጥል እንጥራለን፤ ያ ካልሆነ ደግሞ "ኢፍትህዊ" ነው ብለን እንኮንነዋለን፤ እንዲቀየርም እንታገላለን። የፍትህ እሳቤ ሰውኛ እሳቤ የሆነው ተፈጥሮ ከሰጠችው ውጭ ራሱን የሚደለድለው ሰው በመሆኑ ነው፤ ከሰው ዘር ውጭ የፍትህ ጉዳይ የሚያሳስባቸው ፍጥረቶች ስለመኖራቸው እስካሁን መረጃ የለም።

ምንም ዓይነት ፍትህ የሌለበት ማኅበረሰብን ለማሰብ ብንሞክር በአዕምሮዓችን ሊመጣልን የሚችለው እያንዳንዱ ግለሰብ ወይም በዝምድና የተሳሰረ ስብስብ የገዛ ራሱን ወይም ቡድኑን ለማኖርና ከጥቃት ለማዳን የሚጥርበት ሥርዓት እናገኛለን። በዚህ ሥርዓት ውስጥ "የሥጋ" ዝምድና (ለምሳሌ እናትና ልጅ) ብቸኛው ማስተሳሠሪያ ይሆናል። በሌላ አነጋገር ዘር ብቸኛ የስብስቡ ማስተሳሠሪያ ይሆናል። በማኅበረ-እንስሳት ውስጥ መንጋን የሚያስተሳስረው በዘር መነሻነት የተፈጠረ አብሮ ውሎ ማደር ነው። ፍትህ በሌለበት ማኅበረሰብም ውስጥ የሚዛመዱ ቤተሰቦች ራሳቸው በተለያየ ስያሜ ወደሚጠሩ ስብስቦች ማደግ ይችላሉ። ትልቅም ይሁኑ ትንሽ፣ ስብስቦቹን የሚያገናኛቸው ዝርያቸው ነው። የእንስሳት መንጋ በውስጡ እያንዳንዱ የራሱን ዘርን ለማቆየት በሚያደርገው የደመነፍስ ትግል ውስጥ የሚጠመድ ቢሆንም፣መንጋ በጋራ ደግሞ ለምግብና ለቦታ ከሌሎች መንጋዎች ጋር በማያቋርጥ ትንንቅ ይኖራል። በማኅበረ-እንስሳት ደካማው ብቻ ሳይሆን ጠንካራው መንጋም ቢሆን ከሱ የባሰ ጠንካራ መንጋ እንዳይመጣበት እንደሰጋ ይኖራል።

ፍትህ የሌለበት ማኅበረሰብም እንደዚያው ነው። ፍትህ በሌለበት፣ ሰዎች በዘር መደራጀታቸው ተፈጥሮዓዊ የመሆኑን በኑሮ እድሎች (opportunities) እና ግብዓቶች (resources) ላይ መጣላታቸውም እንደዝያው የማይቀር ተፈጥሮዓዊ ነው። በቡድኖች መካከል ያለው ጦርነት በአንዱ ቡድን ጊዜያዊ አሸናፊነት ጋብ ሲል በቡድኑ ውስጥ ባሉ ቤተሰቦች መካከል ጦርነት ይነሳል፤ ያ ጋብ ሲል ደግሞ በእያንዳንዱ ግለሰብ መካከል ይጀመራል። ሲከፋ ወገንና ጠላት ያልለየ ሁሉም ከሁሉም ጋር (all against all) ጦርነት ውስጥ ይገባል። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ነው ህገ-አራዊት የሚባለው። ፍትህ በሌለበት የሰው ልጆች ሕይወት ወደ ህገ-አራዊት ያሽቆለቁላል።

## 2. ፍትህ፣ ህግ፣ እና የህግ የበላይነት

ፍትህ፣ ህግ፣ እና የህግ የበላይነት በጥብቅ የተቆራኙ ቢሆንም የተለያዩ ጽንሰ-ሀሳቦች ናቸው። ፍትህ፣ ሰዎች ተሳስበው እና ተጋግዘው እንዲኖሩ የሚያደርግ፤ አድልዎንና ጥቃትን የሚከላከል፤ በዳይን የሚቀጣ፣ ተጠቂን የሚክስ ማኅበረሰቡ "ትክክለኛ"፣ "ሚዛናዊ" ወይም "በጎ" የሚላቸው ስነምግባሮች ስብስብ ነው። ፍትህ የማኅበራዊ ተቋማት ውጤት ነው። ህግ "ይህንን አድርግ፤ ያንን አታድርግ" የሚል ድንጋጌ ነው። አቅም ያለው ሁሉ የፈለገውን ህግ አውጥቶ ሊያስፈጽም ይችላል። ህግ መሣሪያ ሲሆን ፍትህ ህጉ በተግባር ላይ ሲውል የሚገኘው ውጤት ነው። ጥሩ ህግ በሥራ ላይ ከዋለ ፍትህን ያስገኛል። ጥሩ ህግ ኖሮ ሥራ ላይ ካልዋለ ህጉ መኖሩ ብቻውን ፍትህን አያስገኝም። መጥፎ ህግ ደግሞ ፍትህን ያጓድላል፤ ኢፍትሃዊነትን ያነግሳል። "የህግ የበላይነት" ሲባል በሁሉም ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ህግ አለ ማለት ነው። የህግ የበላይነት እንዲከበር ቢያንስ ሁለት ነገሮች መሟላት ይኖርባቸዋል፡-

### (1) ህግ፣ ፍትሃዊ ይሁንም አይሁን፣ ያለ አድልዎ በሥራ ላይ መዋል አለበት

መጥፎም ይሁን ጥሩ፣ አንድ ህግ በሁሉም ላይ እኩል ሥራ ላይ ከዋለ የህግ የበላይነትን አንድ መሠረታዊ መሥፈርት አሟላ ማለት

ይቻላል፡፡ በተለይም ህግ አስፈፃሚው በህጎቹ ራሱ የሚገዛባቸው መሆን አለመሆኑ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ ህግ አውጭው የሚያወጣቸውን ህጎች ህግ አስፈፃሚው ሲፈልግ በሥራ ላይ የሚያውላቸው፣ ሳይፈልግ ደግሞ የሚተዋቸው ከሆነ፣ የህጎቹ መኖር ለህግ የበላይነት መከበር የሚሰጠው ፋይዳ የለም፡፡

ዛሬ አገራችን ውስጥ ያለው የህግ ችግር የመጥፎ (የኢፍትሃዊ) ህጎች መብዛት ብቻ አይደለም፡፡ ችግራችን ያለአድልዎ ተፈፃሚ የሚሆኑ ህጎች የመኖርና አለመኖር ጉዳይ ጭምርም ነው፡፡

## (2) የህጎች ፍትሃዊ መሆን አስፈላጊነት

ህግ ሁሉ ግን ወደ ፍትህ አያደርስም፡፡ ፍትህን የሚያሰፍኑ ህጎች አሉ፤ ኢፍትሃዊነትን የሚያሰፍኑ ህጎችም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ የህግና የፍትህ ግንኙነት ውስብስብ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ “ሰዎች ሁሉ እኩል መስተናገድ አለባቸው” የሚል ህግ ቢወጣ በግልቡ ሲታይ ችግር ያለው ባይመስልም በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ግን ፍትሃዊ ላይሆን ይችላል፡፡ አንድ የጤና ጣቢያ ለአንድ የአካል ጉዳት ላለበት ባለጉዳይ እና የአካል ጉዳት ለሌለበት ሌላ ባለጉዳይ እኩል መስተንግዶ መስጠት አለብኝ ቢል ኢፍትሃዊ ነው፡፡ ከሚሰጠው አገልግሎት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የአካል ጉዳተኛው የተለየ መስተንግዶ ሊሰጠው ይገባል፡፡ ከላይ በምሳሌነት የተጠቀሰው ዓይነት በደምሳሳው ሲታይ ችግር ያለበት የማይመስል ቀና ህግ እንኳን በሥራ ላይ በሚውልበት በፍትህ ሚዛን መታየት ይኖርበታል፡፡

> ((ህግ ሁሉ ግን ወደ ፍትህ አያደርስም፡፡ ፍትህን የሚያሰፍኑ ህጎች አሉ፤ ኢፍትሃዊነትን የሚያሰፍኑ ህጎችም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ የህግና የፍትህ ግኑኝነት ውስብስብ ነው፡፡))

ሰው ሆነን ተፈጥረን በሰዎች ማኅበር ውስጥ በማደጋችን ብቻ የተወሰነ የፍትህ ስሜት በውስጣችን አለ፡፡ በዚህ የፍትህ ስሜት (በተለምዶ አነጋገር በህሊና ዳኝነት) የሚገዛ ማንኛውም ሰው በራሱ ላይ እንዲደርስ የማይፈልገውን ነገር በሌሎች ላይ አያደርስም፤ ሌሎች በሌሎች ላይ ጥቃት ሲያደርሱም አይቶ ዝም አይልም፡፡ ህሊናችን ኢፍትሃዊ ህጎችን ይፀየፋል፡፡

## 3. ኢትዮጵያ፣ ህግና ፍትህ

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ በኩል ህግ አክባሪ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ፍትህ የተነፈገ ሕዝብ ነው፡፡ እንዴት ፍትህ የተነፈገ ሕዝብ ህግ አክባሪ ይሆናል? ይህ ለመረዳት የሚቸግር ወለፈንዲ (paradox) ቢሆንም እየኖርን ያለነው እውነት ነው፡፡ ለኢትዮጵያዊያን “በህግ አምላክ” ትልቅ ትርጉም ያለው ሀረግ ነው፡፡ ድሮ ተበዳይ በዳያን አግኝቶ “በህግ አምላክ ቁም ብዬሃለሁ” ካለው ፓሊስ እንኳን ባይኖር ምስክር ወይም ገላጋይ እስኪመጣ ድረስ “ቁም” የተባለው ሰው ባለበት ይቆም ነበር፤ አሊያም ተራ መንገደኛም ቢሆን የሁለቱን ነጠላዎች ቋጥሮ “አቆራኝቶ” ወደ ዳኛ እንዲሄዱ ያደርግ ነበር፡፡ “የህግ አምላክን” ማክበር አምላክን ከማክበር ጋር እኩል ነበር፡፡ “የህግ አምላክ” መኖሩ ተገዢዎች በህጉ ተፈፃሚነት ላይ እምነት እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ ገዢዎችም ቢሆኑ ለዳኝነት ክብር እንዲሰጡ “የህግ አምላክ” በተወሰነ መጠንም ቢሆን አገልግሏል፡፡

ከፍትህ አንፃር የቀደሙት ሥርዓቶች ብዙ ጉድለቶች የነበሩባቸው ቢሆንም ችሎትን እንደ አሁን መዘባበቻ ያላደረጉበት አንዱ ምክንያት ፍትህን ከመለኮታዊ ሥልጣን ጋር ማያያዛቸው ነው፡፡ ይህ እውነታ የኢትዮጵያ ሕዝብ በፍትህ ሥርዓቱ ላይ ከፍተኛ እምነት እንዲያድርበት አድርጓል፡፡ አንድ ባለጉዳይ በአንድ ዳኛ ቢፈረድበት “የህግ አምላክ” ስላለ በሚቀጥለው እርከን ላይ ያለው ዳኛ ዘንድ ፍትህን አገኛለሁ በሚል ለአቤቱታ ይጓዛል፤ እዚያም ባይሳካለት ወደሚቀጥለው እርከን አቤት ይላል፡፡ እንዲህ እያለ አንዳንዱ ንጉሥ ችሎት ዘንድ ይቀርባል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲህ ፍትህ እየተነፈገውም “በህግ አምላክ” ላይ ተስፋ የማይቆርጥ ህገ አክባሪ ሕዝብ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ ህግ አክባሪነት በችሎቶች ደጃፎች ብቻ ሳይሆን በዘወትር ሕይወቱም የሚታይ ነው፡፡ በከተሞች ውስጥ የወርቅ ቤቶችን ግድግዳዎች ተደግፈው የሚያድሩ ድሆች ያሉት ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ጠመንጃ ይዞ “አገሬ መግቢያ መሳፈሪያ ሙሉልኝ” ወይም “ራበኝ፣ ለምሳ ተዘከሩኝ” የሚል ወታደር የነበረው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው፡፡ ይህ ሁሉ መልካም ባህል ዛሬ በዓይኖቻችን ሥር እየተንኮታኮተ ነው፡፡ ይህ በቀላሉ የማይገነባ ክቡር ባህል እያጣን ነው፡፡

አሳዛኙ ነገር በዚህ ህግ አክባሪ ሕዝብ ጫንቃ ላይ የተጫኑ ገዢዎች የሕዝቡን ህግ አክባሪነት በሚመጥን መጠን ህግን አክብረው የሚያስከብሩ አለመሆናቸው ነው፡፡ በህግ አጠባበቅ ረገድ ኢትዮጵያ እየተጓዘችበት ያለው የቁልቁለት ጉዞ አስፈሪ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከአንድ ገገር መዳፍ ወደ ሌላው በተወረወረች ቁጥር ፍትህ ከቀድሞው በባሰ እየተረገጠች መጥታለች፡፡ የቅርቡን ዓመታት እንኳን በምሳሌነት ብንጠቅስ የአጼ ኃይለሥላሴ አገዛዝ ኢፍትሃዊነት ያስመረራቸው ወገኖች ሥርዓቱን ታገሉት፤ በትግሉ አሸንፎ የወጣው ግን ከቀድሞው የባሰው ደርግ ሆነ፡፡ የደርግ ሥርዓት ያስመረራቸው ታገሉት፤ በትግሉ አሸንፎ የወጣው ግን ከደርግ የባሰው የኢህአዴግ አገዛዝ ሆነ፡፡ አሁን በጀመርነው ለውጥ ይህ የቁልቁለት ጉዞ ካልተሰበረ አደጋው በዚሁ ዓይነት ሊቀጥል ይችላል፡፡

ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ የፍትህ እሳቤያችን ራሱ እያሽቆለቆለ መምጣቱ ነው፡፡ ቀድሞ፣ ከላይ እንደተገለፀው፣ ፍትህ መለኮታዊ ፀጋ ተደርጋ ትወሰድ ነበር፤ መቀመጫዋም ከአማልክት ጎን ነበር፡፡ “በህግ አምላክ” ሲባልም የአማልክት መቀመጫ ነው ተብሎ ወደሚታሰበው ሰማይ እየታየ ነበር፡፡ ከማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተዓለም መምጣት

ጋር ፍትህ ከሰማየ ሰማያት ወርዳ መሬት ላይ ተፈጠፈጠች። ፍትህ ሰዎችን ሁሉ በእኩል ማየቷ ቀረና መደባዊ ሆነች። በዚህ አዲሱ ዕይታ መሠረት የላብአደሩ ፍትህ እና የቡርዣው ፍትህ ለየቅል ብቻ ሳይሆን ተቃራኒ ሆነው ተገኙ። ለአንዱ ፍትሃዊ የሆነ ነገር ሁሉ ለሌላው ኢፍትሃዊ ሆነ። ከህወሓት አገዛዝ መምጣት ጋር ደግሞ ፍትህ መደባዊ መሆኗ ቀርቶ ዘውጋዊ ሆነች። በአዲሱ ዕይታ እያንዳንዱ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ የየራሱ ፍትህ አለው። ትግሬው፣ አማራው፣ አሮሞው፣ አደሬው፣ ሶማሌው፣ አፋሩ፣ ሲዳማው፣ ጉራጌው .... እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ፍትህ አላቸው። የኦሮሞው ፍትህ ከትግሬውም ሆነ ከአማራው ሊለይ ይችላል። ለትግሬው ፍትህዊ የሆነ ለአማራው ፍትሃዊ ላይሆን ይችላል። ለምሳሌ አንዱ ክልል ፍትህዊ ነው ብሎ በገነባው ሀውልት በሀሴት ሲጨፍር፤ ሌላው ስሜቱ ክፉኛ ሊጎዳ ይችላል፤ ሶስተኛው ደግሞ ግዴለሽ ሊሆን ይችላል። በአንድ ቋንቋ እየተነጋገርን መስማማት የቸገረንም የፍትህ እሳቤያችን ወደዚህ ደረጃ በመውረዱ ጭምርም ነው።

የፍትህ እጦት በሀገራችን ለሰነፈውና በየጊዜውም እየጨመረ ለመጣው የተበላለጠ (inequality) ሕይወት ምክንያት ሆኗል። ሚሊዮኖች የእለት ጉርስ ባጡበት አገር ውስጥ ጥቂቶች ሀብታቸውን የሚበትኑበት አጥተው ሲጨነቁ ማየት የሚያስቆጭ ነው። ይህ ተበላልጦ ከመንግሥት ስልጣን ጋር ካለ ቅርበት፣ ከብሔር፣ ከጎጥ፣ ከቋንቋና ከሀይማኖትና ጋር ሲዛመድ ደግሞ አደጋው የከፋ ነው። ችጋር፣ ድንቁርና፣ ኃላቀርነት፣ የርስ በርስ መቆራቆሶች - ባጭሩ፤ በአገራችን ያሉ መጥፎ ነገሮች ሁሉ መሠረታቸው ኢፍትሃዊነት ነው። ፍትህ ሲጓደል በደል ይገነግናል፤ ምሬት ይመረቅዛል፤ በውጤቱም ማኅበረሰብ ይናጋል።

## 4. ማኅበራዊ ፍትህ

ከላይ እንደተገለፀው “ፍትህ” ሰዎች ተባብረው፣ ተሳስበው እና ተጋግዘው እንዲኖሩ የሚያደርግ፤ አድልዎንና ጥቃትን የሚከላከል፤ በዳይን የሚቀጣ፣ ተበዳይን የሚክስ ማኅበረሰቡ “ትክክለኛ” ወይም “በጎ” የሚላቸው ስነምግባሮች ስብስብ ነው” ብለናል።

> ‹‹ ማኅበራዊ ፍትህ ከሚለካባቸው መስኮች ቀዳሚዎቹ የሀብት ክፍፍል፣ የአድልዖ መኖርና አለመኖር እና የክብር ጉዳዮች ናቸው።››

“ማኅበራዊ ፍትህ” ማለት ደግሞ በግለሰብ እና በማኅበረሰብ እንዲሁም በማኅበረሰብ ውስጥ ባለ ቡድን እና በማኅበረሰብ መካከል ያለ ግንኙነትን የሚመለከት ነው። ይህ ግንኙነት “ትክክለኛ” ወይም “ተቀባይነት” ያለው ከሆነ ማኅበረሰባዊ ፍትህ ሰፍኗል ማለት ሲቻል፤ ግንኙነቱ ትክክለኛ መስሎ ካልታየ የማኅበራዊ ፍትህ ችግር መኖሩን አመላካች ነው።

ማኅበራዊ ፍትህ ከሚለካባቸው መስኮች ቀዳሚዎቹ የሀብት ክፍፍል፣ የአድልዖ መኖርና አለመኖር እና የክብር ጉዳዮች ናቸው። ለምሳሌ አንድ ድሀ ድሀ ለመሆኑ የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም እንኳን ምክንያቶቹን ሁሉ በሁለት ዋና ዋና ዘርፎች መመደብ ይቻላል። በአንደኛው ወገን ያሉ በራሱ ቁጥጥር ሥር ያሉ ምክንያቶች ሲሆኑ ስንፍና ከእነዚህ አንዱ ሊሆን ይችላል። በሌላ ወገን ደግሞ ከግለሰቡ ቁጥጥር ውጭ ያሉ ምክንያቶች ናቸው። ከእነዚህ ጥቂቶቹ ከድሀ ቤተሰብ መወለዱ፣ ጥሩ ትምህርትና የጤና አገልግሎት አለማግኘቱ ሊሆኑ ይችላሉ። ሁለተኛዎቹ ምክንያቶች የማኅበራዊ ፍትህ መጓደልን የሚያመላክቱ ናቸው።

ማኅበራዊ ፍትህ እንዲሰፍን መታገል ማለት በተቻለ መጠን ዜጎች የሀገር ሀብትና እድሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል ማለት ነው። ይህ ማለት ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ለመዋቅራዊ በደል ተጋልጠው የነበሩ ዜጎችን ከተጫነባቸው በደል ማላቀቅ ማለት ነው። ይህ ደግሞ በአካል ጉዳት ወይም በማኅበራዊ ቀውስ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ወገኖችም የዕድሉ ጠቃሚ እንዲሆኑ ልዩ ድጋፍ መስጠትንም ያጠቃልላል። ማኅበራዊ ፍትህ በቁሳዊ ጉዳዮች ብቻ ሳይሆን ቁሳዊ ባልሆኑ ህሊናዊና ስነልቦናዊ ጉዳዮችንም ይመለከታል። ሰው በቆዳው ቀለም፣ በቁመቱ፣ በጾታው፣ በእድሜው፣ በአካል ብቃቱ፣ በጤንነቱ፣ በሀይማኖቱ፣ በቋንቋው፣ በሙያው፣ በዘሩ ወይም በሌላና እነዚህን በመሳሰሉ የማንነት መገለጫዎች ሳቢያ መድልዖ እንዳይደርስበት መከላከል የማኅበራዊ ፍትህ አብይ አጀንዳ ነው። ከላይ በተዘረዘሩት የማንነት መገለጫዎች ሳቢያ ለመድሎ ለተጋለጡ ዜጎች የተለየ ድጋፍ መስጠትም የማኅበራዊ ፍትህ አንዱ ግብ ነው። ከዚህ አልፎ አንድ ትውልድ በመጪው ትውልድ ላይ እዳ አስቀምጦ ማለፉም ማኅበራዊ ፍትህ የጎደለው አሠራር ነው። ይህ የሀብት አጠቃቀምን ብቻ ሳይሆን የአካባቢ ጥበቃንም (physical enviroment) ይመለከታል። መደብ፣ ብሔር፣ ቋንቋ፣ ክልል፣ ሀይማኖት፣ጾታ፣ ዕድሜ፣ የአካል ጉዳት እና በመሳሰሉት ምክንያቶች የሚደርሱ በደሎች መነሻ የማኅበራዊ ፍትህ ጉድለት ነው።

ማኅበራዊ ፍትህን ማስፈን ዜጎች ተፈጥሮ የሰጠቻቸውን ችሎታዎች ተጠቅመው ራሳቸውን፣ ቤተሰባቸውን፣ ማኅበረሰባቸውና ሀገራቸውን ከዚያም አልፎ መላውን ዓለም ለመጥቀም ሰፊ እድል ይከፍትላቸዋል።

ማኅበራዊ ፍትህ በግለሰብ (ዜጋ) እና በኅብረተሰቡ መካከል መኖር የሚገባቸው

ግንኙነቶች ሁሉ ሁለቱንም ወገን እኩል የሚመለከቱ ፍትሃዊ ግንኙነቶች መሆን አለባቸው የሚል ጽንሰ-ሀሳብ ነው፡፡ እነዚህ ግንኙነቶች ደግሞ የዘፈቀደ ግንኙነቶች ሳይሆኑ በተግባራዊነታቸው ግልጽ በሆኑ የሃብት፣ የሥራ እና የትምህርት ዕድል ክፍፍልና በአጠቃላይ ዜጎች በሀገራቸው ጉዳይ ላይ ከሚያደርጉት ነጻ የፖለቲካ ተሳትፎ ባሻገር በኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፍም በሚያደርጉት ተሳትፎና በሚያገኙት ዕድል መጠን በሚለካ ግንኙነት ነው፡፡ ዛሬ በአንዳንድ ያደጉ ሀገሮች ውስጥ ማኅበራዊ ፍትህ ብለው የሚጠሩት ብዙውን ጊዜ ግለሰቦች ማኅበራዊ ሚናቸውን መወጣት እስከቻሉ ድረስ ከማኅበረሰቡ ማግኘት የሚገባቸውን ማግኘት ይችላሉ የሚል ነገር ግን ለማግኘታቸው ምንም ዋስትና የማይሰጥና ባለው እና በሌለው መካከል ትልቅ ልዩነት የሚፈጥር ከፍትህ የራቀ ሂደት ነው፡፡ በአንድ ሀገር ውስጥ ማኅበራዊ ፍትህ ሰፍኗል ማለት የሚቻለው የመንግሥት የኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ ፖሊሲዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ የተመጣጠነ የሀብት እና ማኅበራዊ አገልግሎት ክፍፍል እንዲኖር የሚያስችሉ ሆነው ሲቀረጹ ነው፡፡ ለማኅበራዊ ፍትህ ቅድሚያ በሚሰጡ ሀገሮች ውስጥ የግብር፣ የማኅበራዊ ዋስትና፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የማኅበራዊ አገልግሎት፣ የሠራተኞች እና የገበያ ቁጥጥር ተቋሞች እያንዳንዱ ዜጋ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚገኘውን ጥቅም እና ሸክም በተመጣጠነ መልኩ እንዲጋራ ማድረግ በሚችሉበት መልኩ የሚደራጁ መሰረታዊ ተቋሞች ናቸው፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ ማኅበራዊ ፍትህ ዜጎች እኩል ናቸው ስለተባለ ብቻ እኩል አይሆኑም፤ የዜጎች እኩልነት የሚረጋገጠው እኩልነትን ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ ተደርገው የሚዋቀሩ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተቋሞች ሲኖሩ ብቻ ነው የሚል ትልቅ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ መርህ ነው፡፡

## «በአንድ ሀገር ውስጥ ማኅበራዊ ፍትህ ሰፍኗል ማለት የሚቻለው የመንግሥት የኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ ፖሊሲዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ የተመጣጠነ የሀብት እና ማኅበራዊ አገልግሎት ክፍፍል እንዲኖር የሚያስችሉ ሆነው ሲቀረጹ ነው፡፡»

## 5. ኢዜማ እና ማኅበራዊ ፍትህ

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ ፓርቲ የማኅበራዊ ፍትህ መስፈን ለሀገራችን እድገት ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ ፕሮግራሙን የቀረፀ ፓርቲ ነው። ፓርቲያችን ለማኅበራዊ ፍትህ የሰጠውን ከፍተኛ ቦታ በፕሮግራሙ በዝርዝር ያስቀመጠ ቢሆንም የሚከተሉት የመግቢያ ዓረፍተ ነገሮች ለአብነት ያህል ቀርበዋል።

### 5.1. የኢዜማ የፓለቲካ ፕሮግራም መግቢያ

"የፓርቲያችን የፖለቲካ ፕሮግራም በወሳኝ መልኩ ያልተማከለ አስተዳደር (ፌዴራላዊ) ሥርዓትን መከተለን ምርጫው ያደረገ ነው። ከፍተኛው የመንግሥት ኃላፊነት በሕዝብ ቀጥታ ምርጫ የሚመረጥ ፕሬዝዳንታዊ ሥርዓት እንዲሆን አበክሮ ይሰራል፡፡ ፓርቲያችን የሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነት በማረጋገጥ፤ ዜጎች ከማኅበራዊ ፍትህ እሳቤ የሚመነጩ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ፖሊሲዎች የሚከተል ፕሮግራም ከሚገኝ ትሩፋት ተጠቃሚ ይሆናሉ ብሎ ያምናል፡፡ ፓርቲያችን ሕገ መንግሥት ማሻሻያ በሥርዓት በማድረግ፤ ዜጎች ያለተፅእኖ ተሳትፎ ያደረጉበት፣ የመንግሥትን ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ እንዲሆን በትጋት ይሠራል።"

### 5.2. የኢዜማ የኢኮኖሚ ፕሮግራም መግቢያ

"ፓርቲያችን ከሚከተለው የፖለቲካ ፍልስፍና /ማኅበራዊ ፍትህ/ ጋር የሚጣጣም ለዜጎች ኤኮኖሚያዊ ነፃነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ የኤኮኖሚ ፕሮግራም እና ፖሊሲዎችን ይቀርፃል። ፓርቲያችን የመንግሥት የኤኮኖሚ ባለቃንብነት ሊኖር የሚችልባቸውን ዘርፎች በመለየት በግልፅ የሚያስቀምጥ ሲሆን በማንኛውም ሁኔታ ከዜጎች ጋር መንግሥት ውድድር ውስጥ ሊገባ የሚችልበት እድል አይኖርም።"

### 5.3. የኢዜማ የማኅበራዊ ፕሮግራም መግቢያ

"የፓርቲያችን ማኅበራዊ ፕሮግራም ዓላማ፤ ዜጎች በተበላሹ የመንግሥት ፖሊስ በመገፋት ከኤኮኖሚ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ እንዲርቁ የተደረጉ ብቻ ሳይሆን በዚሁ መነሻ ለከፍተኛ ማኅበራዊ ቀውስ የተዳረጉ ዜጎችን በስርዓቱ ውስጥ ለማካተት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡ ዜጎች በማኅበራዊ ዘርፍ ፓርቲያችን የሚወስዳቸውን ተጨባጭ እርምጃዎች በመጠቀም ራሳቸውን ጠቅመው ለሀገር የሚተርፉ ዜጎች ማድረግ የማኅበራዊ ፕሮግራማችን ቀዳሚ ትኩረት ነው። የፓርቲያችን ፕሮግራም በምንም መልኩ ሥራ ጠልነት እና ድጋፍ ጠባቂነትን አያበረታታም፣ ዝርዝር ፖሊሲዎችም ይህን ታሣቢ ያደረጉ ይሆናሉ።"

# ኢዜማ ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት ያስተላልፋል

ነሐሴ 30 ቀን 2011 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የፊታችን ቅዳሜ ጳጉሜ 02 ቀን 2011 ዓ.ም በመላው አዲስ አበባ ከተማ እየተዟዟሩ ለአዲስ አበባ ነዋሪ የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት እንደሚያስተላልፉ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የዓለም ዓቀፍ አባላት ተጠሪ ኢዮብ መሳፍንት ገለፁ፡፡

ለዚህ መርሃ ግብር በርካታ መኪኖች እንደተዘጋጁና በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ 23ቱም የምርጫ ወረዳዎች በፕሮግራሙ ላይ ተሳታፊ እንደሚሆኑበት ተጠሪው ገልፀዋል፡፡ የፕሮግራሙ ዋና አላማ ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ አዲሱን ዓመት ተከትሎ የመልካም ምኞት መልእክት ለማስተላለፍና ኢዜማንም ለማስተዋወቅ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ኢዜማ ባሳለፍነው ቅዳሜ ነሐሴ 25 ቀን 2011 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ወጣቶች ጋር በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ውይይት ማካሄዱ የሚታወስ ሲሆን፣ ይህኛው መርሃ ግብር ከአዲስ አበባ ነዋሪ ጋር ለሁለተኛ ጊዜ የሚያገናኘውና ራሱንም ከአዲስ አበበ ነዋሪዎች ጋር የሚያስተዋውቅበት መድረክ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

---

# የኢዜማ አዳማ ምርጫ ወረዳ 3 ጽሕፈት ቤት ከፈተ

ነሐሴ 30 ቀን 2011 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ የአዳማ ምርጫ ወረዳ 3 ጽሕፈት ቤት መከፈቱን የምርጫ ወረዳው አስተባባሪ የሆኑት ዘሪሁን ደበሌ ገለጹ፡፡

በኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ 3 የምርጫ ወረዳዎች እንዳሉ የገለጹት አስተባባሪው ዘሪሁን ደበሌ በሶስቱም የምርጫ ወረዳዎች መዋቅሮች ተዘርግተው የቀበሌ መዋቅር አደረጃጀቶችን በመሠራት ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡ ሆኖም ሥራዎችን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማካሄድ ቢሮ አለመኖሩ ችግር እንደፈጠረባቸው እና ችግሩን ለመቅረፍ በአዳማ ከተማ መብራት ኃይል አካባቢ ምንጭ የገበያ ማዕከል በከተማው የመጀመሪያውን ጽሕፈት ቤት መክፈት መቻላቸውን አስተባባሪው ገልጸዋል፡፡ በአዳማ ከተማ የሚገኙት ሌሎች ሁለት ምርጫ ወረዳዎች የራሳቸው ጽሕፈት ቤት እስኪከፍቱ ድረስ በጋራ የማስተባበር ሥራ አሁን በተከፈተው ጽሕፈት ቤት እንደሚሠሩ ነው አስተባባሪው ያሳወቁት፡፡

በተያያዘ ዜና ባለፈው ቅዳሜ ነሐሴ 25 በስሬ ወረዳ ይደረጋል ተብሎ የነበረው ሕዝባዊ ስብሰባ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለመጪው ቅዳሜ ጷግሜ 2 ቀን 2011 ዓ.ም መዘዋወሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

# ኢዜማ ከአዲስ አበባ ወጣቶች ጋር ውጤታማ ውይይት አካሄደ

ነሐሴ 30 ቀን 2011ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)





የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ከአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች ጋር ነሐሴ 25 ቀን 2011 ዓ.ም ሰፊ ሕዝባዊ ውይይት በተሳካ ሁኔታ ማካሄዱን የወጣቶች ጉዳይ ተጠሪ ቴዎድሮስ አሰፋ ገለጹ፡፡

በዕለቱ የሚጠበቀውን ያህል ወጣት በውይይቱ ላይ መሳተፉን እና ያለገደብ ከታዳሚው ጥያቄዎች ቀርበው መድረኩን ይመሩ ከነበሩ አመራሮችም በቂ ምላሽ መሰጠቱን እና በውይይቱ ላይ ከተሳታፊዎች ትኩረት እንዲሰጣቸው የተጠቆሙ ጉዳዮችን አመራሮቹ መቀበላቸውን የወጣቶች ጉዳይ ተጠሪው ጨምረው ገልጸዋል፡፡

በውይይቱ ላይ ‹‹ ኢዜማ ለምን በሀገራችን የሚከሰቱ ጉዳዮች ላይ ቶሎ አቋሙን የሚገልጽ መግለጫ አያወጣም?›› በሚል ለተነሳው ጥያቄ ‹‹መጀመሪያ መግለጫ የሚሰጥበት ጉዳይ እውነትነቱ ተረጋግጦ፣ መግለጫ በመስጠቱ ተጨማሪ ጉዳት አለማምጣቱን አመዛዝነን እና እኛ መንግሥት ብንሆን ምን ልናደርግ እንችል ነበር? የሚሉትን አጢነን መግለጫ መስጠቱ ተገቢ መሆኑን ስናውቅ ብቻ ነው መግለጫ የምንሰጠው፡፡›› ሲሉ የኢዜማ ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋ አብራርተዋል፡፡

የአዲስ አበባ ተወላጆችን የሚያገል ፖሊሲ እንዳለና የአዲስ አበባ ልጅ በሁሉም ቦታ ወኪል አጥቷል፣ ለዚህ መፍትሄ አላቹህ ወይ? በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስትያን ላይ እየተቃጣ ያለው አደጋ ላይ ኢዜማ ምን አቋም አለው? ኢዜማ ከአዲስ አበባ ባለፈ በክልል ላይ ያለው አደረጃጀቱ ምን ያህል ነው? የሚሉ ተጨማሪ ጥያቄዎችም በውይይቱ ተሳታፊ ከነበሩ ወጣቶች ተነስቷል፡፡

በአዲስ አበባ ወጣት ላይ ያለውን መገለልና ጫና ኢዜማ እንደሚታገል፤ ከቤተክርስቲያን መቃጠል ጋር በተያያዘ ለተነሳው ጥያቄ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን መስጂድም ሌሎች የእምነት ተቋማትም ላይ የሚደርስ ጥቃት ኢዜማ እንደሚያወግዝ እና የዜጎች የእምነት ነጻነት በሚገባ መከበርን ኢዜማ በጥብቅ ከሚቆምላቸው ነጻነቶች መካከል እንደሆነ በማስረገጥ ከመድረክ ምላሽ ተሰጥቷል፡ ፡ በአሁኑ ወቅት ኢዜማ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ ቦታዎች 400 የሚጠጉ የምርጫ ወረዳዎችን ማደራጀቱን እና የምርጫ ወረዳዎቹ እራሳቸውን እንዲያጠናክሩና ተጨማሪ የምርጫ ወረዳዎችን ለማዳረስ እንቅስቃሴ እየተደረገ እንደሆነ አመራሮቹ ጨምረው አብራርተዋል፡፡

ከውይይቱ በኋላ የወጣቶች ጉዳይ ተጠሪው ቴዎድሮስ አሰፋ እንደገለፁት፤ ውይይቱ በተሳካ ሁኔታ የተካሄደ ሲሆን ኢዜማ ከተመሠረተ በኃላ ከኅብረተሰቡ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ መገናኘቱን በመግለጽ በቀጣይም የሕዝባዊ ውይይትና ኢዜማን የማስተዋወቅ ሥራ ላይ ትኩረት ሰጥተው እንደሚሠሩ አሳውቀዋል፡፡ አያይዘውም ኅብረተሰቡ ነገሮችን በማስተዋል፣ የውይይትና የንግግርን ባህሉን ሊያዳብር እንደሚገባው ገልጸዋል፡፡

# በፌደራሊዝም ዙሪያ ስልጠና ተሰጠ

ነሐሴ 30 2011 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የአዲስ አበባ ምርጫ ወረዳ 16 ለሥራ አስፈፃሚዎችና የቀበሌ አደራጆች በፌደራሊዝም ጽንሰ ሀሳብባና የመንግሥት መዋቅራዊ ቅርፆች ዙሪያ እሁድ ነሐሴ 26 ቀን 2011 ዓ.ም በወረዳው ጽሕፈት ቤት ሥልጠና ተሰጠ፡፡

ሥልጠናውን የሰጡት ኤፍሬም ማዴቦ ‹‹ፌደራሊዝም ማለት ራስን በራስ ማስተዳደርና የጋራ አመራር መስጠት መሆኑን ጠቅሰው፣ ሀገራችን ከሚጠብቋት ሶስት ትልልቅ ህገ መንግስታዊ ምርጫዎች ውስጥ አንዱ የመንግሥት መዋቅር ምርጫ ነው፡፡›› ብለዋል፡፡ አያይዘውም ‹‹ኢትዮጵያን የመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የእርስ በእርስ ግጭትና የፖለቲካ ቀውስ ተላቀው ዴሞክራሲያዊ ሽግግር የሚያደርጉ ሀገሮች የሚመርጡት የመንግሥት ዓይነት፣ የመንግሥት ቅርፅና የምርጫ ሥርዓት ዓይነት በሀገሮቹ የረጅምና የአጭር ግዜ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ እጅግ በጣም ከፍተኛ ሚና ይጫወታል›› ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በሥልጠናው ተሳታፊ ከነበሩት የወረዳው ሥራ አስፈፃሚዎች መካከል የምርጫ ወረዳው ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ሳሙኤል ማሞ ‹‹የዚህ ሥልጠና አስፈላጊነት እጅግ የጎላ ነው፡፡ ተመሣሣይ ሥልጠናዎች ቢዘጋጁ የወረዳው ሥራ አስፈጻሚም ሆነ የቀበሌ አደራጆች ስለ ፓርቲው መሠረታዊ መርሆችና ፖለቲካዊ ፅንሰ ሀሳቦች በቂ እውቀትን ሰንቀው የተማሩትን ለማስተማር የሚያስችል አቅም ለመፍጠር ይረዳናል›› ብለዋል፡፡